# ሰሞነኛ

## የሚያበረታታ መልካም ጅምር

አገራችን ቀስፈው ከያዟት መጠነ ሰፊ ማህበራዊ ፣ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመለቃቅ የሚያስችሏት የተለያዩ ፖሊሲዎች ነድፋ ቀና ደፋ በማለት ላይ ትገኛለች:: እንደ ኢትዮጵያ ባለች ዙሪያ መለስ ችግር ተብትበው በያዟት አገር ሁሉንም የእድገት አማራች ሳትመርጥ መጠቀም ይኖርበታል:: ይህንም መርህ ተግባራዊ ለማድረግ የልማት ሃይል የሆኑ ወገኖችን ሁሉ ሳያሰልሱ መጠቀም ይገባል:: የኢትዮጵያ መንግስት ቅድሚያ በሰጠባቸው በምግብ ራስን በመቻልና ድህነትን በማስወገድ መርሆዎች ተፈፃሚነት መንግስት ፣ የግል ባለሀብቱና የኢትዮጵያ ህዝብ ዋነኛ የልማት ሀይሎች መሆናቸው ተደጋግሞ ተጠ ቅ ሷል::

በዚህም መሰረት መንግስት ስላምና መረጋጋትን ከማስፈን ባሻገር፣ለዕድገታችን የሚበጁ ህጎችንና ፖሊሲዎችን ማውጣት፣አገሪቱን በእኩልነትና በአንድነት ማስተዳደር ፣ ወዘተ ያከናውናል::ይህም ብቻ ሳይሆን የግል ባለሀብቱ ሊሳተፍበት ባልቻለባቸውና ለህዝቡ መሰረታዊ አገልግሎት በሚቀርብባቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች ውስጥ የጎላ ሚና በመጫወት የተጀመሩ የልማት ተግባራት ሳይቆራረጡ በቀጣይነት እንዲከናወኑ የዕድገት ሞተር በመሆን ያገለግላል::

በተለይም በአገራችን የግል ባለሀብቱ በቀድሞው ህ/ሰባዊ ስርዓት ምክኒያት ተደፍቆ የቆየና ልማታዊ ሚና ለመጫወት የአቅምና የገንዘብ ውሱንነት ያለበት በመሆኑ የመንግስትን ሚና የጎላና ሚዛናዊ እንዲሆን ያደርገዋል::

በአገራችን ባለፉት አሥር አመታት የተደረገውም ይኸው ነው:: መንግስት የግል ባለሀብቱ ሊሰማራባቸው የሚችሉትን መስኮች በመለየት ሰፋፊ ድጋፎች ሲሰጥ ቆይቷል::ከዚሁም ጋር በአገራችን በብዛትና በአስተማማኝነት ደረጃ የሚገኙትን መሬትና የሰው ጉልበትን ውጤታማ በሆነ መልክ በመጠቀም የሚያበረታቱ ስራዎች ተከናውነዋል ::በዚህም ምክኒያት አሁን ተገኘ የምንለው 10.5 የኢኮኖሚ ዕድገት እነዚህን የልማት ሀይሎች ውጤታማ አድርጎ በመምራት እረገድ የተገኘ ስኬት ነው ልንለው እንችላለን::

የጀመርናቸውን የልማት እድገቶች በተጠናከረ ህዝባዊ ተሳትፎ የጎለበቱ ይሁኑ እንጂ፣ መሰረታቸው እየሰፋና የአስተማማኝነት ደረጃቸው ከማይቀለበስበት ደረጃ ለማድረስ አሁንም የህዝባዊ ተሳትፎ መጠናችን መጨመርና መዳበር ይገባዋል::



Bi-monthly news bulletin prepared by the Consulate General of Ethiopia
3460 Wilshire Blvd#308 Los Angeles, CA 90010
Tel: 213-365-6651 Fax: 213-365-6670 info@ethioconsulate-la.org
www.ethioconsulate-la.org

# ሰሞነኛ

በህዝባዊ ተሳትፎ ዙሪያ በአገርቤት የሚገኘው ህዝብ ዋነኛ የልማቱ ሞተር ባለቤት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣በውጭ የሚገኘው ወገናችን ደግሞ የበኩሉን ቁልፍ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል:: በውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊና ትውልድ ኢትዮጵያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢንቨስትመንት፣በንግድ፣ በማህበራዊ አገልግሎቶች ግንባታና መንግስታዊ ባልሆኑ የተለያዩ ድርጅቶች የሚያደርገው ተሳትፎ እየጨመረ በመምጣት ላይ ነው:: በአዲስአበባና በክልሎች ከመኖሪያ ቤት ግንባታ እስከ ታላላቅ የኢንቨስትመንት ግንባታዎች የተጀመሩ የልማት ተግባራት የሚያሳዩት ፣በውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊና ትውልድ ኢትዮጵያዊ በሚያስማሙ ተግባራት በመቀራረብ የአገርን ገፅታ ለመለወጥ ቆርጦ መነሳቱን ነው:: ከሁሉም በላይ በአገራችን የሚታየውን የማህበራዊ አገልግሎቶች ችግርን ለማቃለል አቅም በፈቀደ መጠን በት/ቤት ግንባታ ፣ በክሊኒክና ጤና ጣቢያ ግንባታ ፣ በመፅሐፍትና የህክምና ቁሳቁስ ዕርዳታ ወ. ዘ.ተ የሚደረገው እንቅስቃሴ ለወገን ደራሹ ወገን ነው የሚለውን ብሂል ዕውን መሆኑን ይመሰክራል::

በውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ለተወለደባቸውና ላደገባቸው አካባቢዎች እንዲሁም ለተማረባቸው ት/ቤቶች ገንዘብ በማዋጣት የማስፋፊያ ግንባታ እንዲከናወኑ እንዲሁም ቤተ መፅሐፍት እንዲደራጁ በጎ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛ ል::እነዚህ ወገኖች በተለያየ የልማት ማህበራት በመሰባሰብ እያደረጉ ያለው እንቅስቃሴ እስከ አሁን የረባ አስተዋፅኦ ያላበረከቱ ወገኖችን ራሳቸውን እንዲመረምሩ የሚያደርግ ነው::

በተለይም በትግራይ ልማት ማህበር ስር የተለያዩ ህዋሶችንና በመመስረት እየተደረገ ያለው ተግባር ለሌሎቻችን ትምህርት ሊሆን የሚገባ ተግባር በመሆኑ እዚህ ላይ ማንሳት ወቅታዊ ነው ብለን እናስባለን::

በም/ዩናይትድ ስቴትስ በተለያዩ ከተማዎች (ሳንሆዜ፣ ኦክላንድ፣ሳንዲያጎ፣ወ.ዘተ) የትግራይ ተወላጆች ገንዘባቸውን በመደበኛ መልክ በማዋጣት የተለያዩ የ1ኛ ደረጃ ት/ቤቶችን በመስራት ላይ ይገኛሉ::ለምሳሌ የሳንዲያጎ ቻፕተር በማይፀምሪ ወረዳ የሚገኝ ት/ቤት እየሰራ ሲሆን፣ የሳንሆዜ ቻፕተር ደግሞ በሽሬ ወረዳ የሚገኝ ት/ቤት በመስራት ላይ ይገኛ ል::ሌሎችም ቻፕተሮች እንዲሁ በየገጠሩ ት/ቤትና ጤና ኬላ በማስገንባት ላይ የሚገኙ ሲሆን ፣ ይህም እድገትን በተባበረ ህዝባዊ ተሳትፎ ዕውን ማድረግ እንደሚቻል ያመለክታል::



Bi-monthly news bulletin prepared by the Consulate General of Ethiopia
3460 Wilshire Blvd#308 Los Angeles, CA 90010
Tel: 213-365-6651 Fax: 213-365-6670 info@ethioconsulate-la.org
www.ethioconsulate-la.org

# ሰሞነኛ

በጎንደር ልማት ማህበር (ጎልማ) ከፋሲለደስ አጠ/2ኛ ደረጃ ት/ቤት ማስፋፋት እስከ ጎንደር ሆስፒታል የግንባታ ውጥን የሚታየው የልማት ርብርብ በውጭ የማገኘው ጎንደሬ ከወገኑ ጋር ያልተለየ መሆኑን ያመለክታል :: የአዘዞ አካባቢ ተወላጆችም ከት/ቤት ማስፋፋት እስከ ሲፖርት ቁሳቁስና መፅሀፍት ዕርዳታ ድረስ የማዳርጉት የልማት ተሳትፎ ጅምሩ አበረታች ነው:: በቅርቡም የደባርቅ ተወላጆች በደባርቅ ወረዳ አካባቢ ት/ቤቶች ለማስፋፋት፣የመንገድ መብራቶችን ለመትከልና የህሙማን ማመላለሻ አንቡላንስ ለማቅረብ የያዙት አላማ በእጅጉ የሚደነቅና ሊበረታታ የሚገባው ጉዳይ ነው::

በሎስአንጀለስ የሚገኙት የሀረሪ ኮሚኒቲ አባላትም በሀረር ከተማ በሚካሄደው ሁለንተናዊ እድገት በተለያየ መንገድ ይሳተፋሉ::ይህም የሀረር ከተማ

ወቅታዊ ችግር ከነበረው የመጠጥ ውሃ ችግር ጀምሮ የኮሚኒቲ አባሎቻቸውን የት/ቤት ቁሳቁስ እስከ መደገፍ የሚደረስ ተግባር ያከናውናሉ::

ሌሎቻችንስ ? በየተወለደንበትና ባደግንበት አካባቢ ማህበራዊ ችግሮችን ለማቃለል ምን ያህል ተንቀሳቅሰናል? ወይስ ለየአካባቢያችን ችግር ከከንፈር መጠጣ ያለፈ ማድረግ አልቻልንምን? የአማራው ክልል ተወላጆች በየልማት ማህበራት ተደራጅተን አካባቢያችን ከመደገፍ የሚያግደን ነገር ምንድን ነው? የደቡብስ? የኦሮሞስ? እነዚህ ጥያቄዎች ለየክልላችን ብሎም ለአገራችን በጎ በጎውን ለምናስብ ሁሉ ልናጤናቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው::

«ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ ነው ለሃምሳ ሰው ግን ጌጡ ነው» እንደሚባለው ሁሉንም የልማት ተግባራት በመንግስት ብቻ ይከናወናሉ ብሎ መጠበቁ ከገን ዘብና ከሰው አቅም አንጻር የሚቻል ባለመሆኑ የህዝቡ የልማት ተሳትፎ ወሳኝና ትክ የማይገኝለት ያደርገዋል::

በመሆኑም በተለያየ ምክኒያት ከአገር ቤቱ ልማት ራሳችሁን ያገለላችሁና ትርጉም ያለው ተሳትፎ ከማደረግ የታቀባችሁ ወገኖች በልማት አደረጃጀቶች በመሰባሰብ በኢትዮጵያ የተጀመረውን ፈጣን የልማት ጉዞ እንድትቀላቀሉ የሎስአንጀለስ ቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት ጥሪውን ያስተላልፋል::

ለዚህ ሰናይ ተግባር ለምታድርጉት እንቅስቃሴ ሁሉ አስፈላጊው ድጋፍ የማይለያችሁ መሆኑንም በዚሁ አጋጣሚ እናረጋግጣለን::



Bi-monthly news bulletin prepared by the Consulate General of Ethiopia
3460 Wilshire Blvd#308 Los Angeles, CA 90010
Tel: 213-365-6651 Fax: 213-365-6670 info@ethioconsulate-la.org
www.ethioconsulate-la.org